# ከጥሬ ገንዘብ ነፃ የሆነ በውስን ቦታ-ማቆሚያ የአውቶቡስ አገልግሎት ምን ያስባሉ?

ሜትሮ የአውቶቡስ አገልግሎትን የማፋጠን ዘዴዎችን እየተመለከተ ነው። በውስን ቦታ-ማቆሚያ መስመሮችን በጥሬ ገንዘብ ሳይሆን አስቀደሞ በተጫነ ስማር ትሪፕ® ካርድ ብቻ ለማስከፈል እያሰበ ነው።

ተሳፋሪን ማሳፈር እና ክፍያ መቀበል እስከ 25% የአውቶቡስ መስመር የመጓጓዣ ሰዓትን ሊወስድ ይችላል። በጥሬ ገንዘብ ክፍያዎች ከስማር ትሪፕ® መምታት የበለጠ ረዥም ጊዜ እንደሚወስድ በጥናት ታይቷል።

አሁን በሀሳብ ላይ ያሉት የውስን ቦታ-ማቆሚያ መስመሮች የሚከተሉት ናቸው፣ 16Y, 37, 39, 59, A9, G9, J4, K9, S9, X9, REX, እና ሜትሮዌይ፣ እንዲሁም የወደፊት የውስን ቦታ-ማቆሚያ መስመሮች። Route 79 MetroExtra በአሁኑ ጊዜ ለሙከራ ከጥሬ ገንዘብ ክፍያ ነፃ ነው። የአካባቢ መስመሮች ጥሬ ገንዘብ መቀበል ይቀጥላሉ።

**አስተያየትዎን በአካል ወይም በኦንላይን እስከ ሰኞ፣ መስከረም 24 ቀን 2018 ዓ.ም.፣ 9:00 a.m. ድረስ ይስጡን።**

ቃለ መጠይቁን ለመውሰድ እና አስተያየትዎን ለመስጠት በኦንላይን **wmata.com/bus** ይግቡ።

በልዩ ዝግጅት በ 6:30 p.m. እና የሕዝብ መደመጥ ከ 7:00 p.m. ጀምሮ በሜትሮ ዋና መሥሪያ ቤት፣ 600 5th Street NW, Washington DC፣ ሰኞ፣ መስከረም 17 ቀን 2018 ዓ.ም. ይካፈሉ። የተናጋሪዎቸ ምዝገባ በቦታው ብቻ ሲሆን፣ ከመጨረሻው ተናጋሪ በኋላ ይዘጋል።

የሜትሮ ቦርድ ዲሬክተሮች ህዳር 2018 ለመጨረሻ ጊዜ ለሚያደርጉት ውሳኔ ሂደት የሕዝብ አስተያየት ይሰጣል። በፌደራል የመጓጓዣ አስተዳደር መመሪያ መሠረት፣ ሜትሮ ማንኛውንም ቋሚ የሆነ በጥሬ ገንዘብ ክፍያ አማራጭን ከማስቀረቱ በፊት ተጨማሪ የሕዝብ ተደራሽነት እና የአንቀጽ 6 ትንተና ያካሂዳል።

የሕዝብ ተሳትፎ ካለምንም የዘር፣ የቀለም፣ የብሔር፣ የዕድሜ፣ የፆታ፣ የኃይማኖት፣ የአካል ጉድለት ወይም የቤተሰብ አቋም ልዩነት ይጠየቃል። በአካል ጉዳተኞች አሜሪካኖች ድንጋጌ መሠረት የተለየ መስተንግዶ ወይም የትርጉም አገልግሎቶች (በነፃ) ካስፈለገዎት ለፕሮጀክት ቡድኑ ቢያንስ ከ48 ሰዓት በፊት በ 202-962-2511 (TTY: 202-962-2033) ይደውሉ።

**ለበለጠ መረጃ፣ በድህረ ገጽ wmata.com/bus ይመልከቱ።**